የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 28
ADDIS ABABA 24th March 2009

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፷፬/፪ሺ፩

የገቢ ግብር /ማሻሻያ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ገፅ ፬ሺ፮፻፷፯

## CONTENTS

Regulation No. 164/2009

Council of Ministers Income Tax (Amendment) Regulation........................................ Page 4667

**ደንብ ቁጥር ፩፻፷፬/፪ሺ፩**

**የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል በማስፈለጉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፩፻፲፯ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የገቢ ግብር (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፬/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር ፸፰//፲፱፻፺፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩. የደንቡ አንቀጽ ፲፪ ድንጋጌ ተሠርዞ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"፲፪. ኪሣራን ስለማሸጋገር

፩. በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ በተደነገገው መሠረት ኪሣራ ሊሸጋገር የሚችለው ኪሣራ የሚያሣየው የሂሣብ መዝገብ በግብሩ ባለሥልጣን ኦዲት ተደርጎ ተቀባይነት ሲያገኝ ይሆናል፡፡

Regulation No. 164/ 2009

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE INCOME TAX REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005, and Article 117 (1) of the Income Tax Proclamation (as amended) No. 286/2002.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Income Tax (amendment) Regulation No. 164/2009."

2. *Amendment*

The Council of Ministers Income Tax Regulation No. 78/2002 is here by amended as follows.

1. The provision of Article 12 is repealed and amended by the following new Article12.

"12.) *Loss Carry Forward*

1. For purposes of Article 28 of the Procla-mation loss may be carried forward where the books of account showing the loss is audited and accepted by the Tax Authority.

፪. የግብሩ ባለሥልጣን እስከቀጣዩ የግብር ዘመን የገቢ ማስታወቂያ ጊዜ ድረስ ኪሣራ የሚያሳየውን የሂሣብ መዝገብ መመርመር መቻል አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ኪሣራ ያሳየውን የሂሣብ መዝገብ መመርመር ካልቻለና ግብር ከፋዩ በውጪ ኦዲተር የተመረመረ ሂሣብ ካቀረበ ኪሣራው መሸጋገር ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ በተመለከተው መሠረት በውጪ ኦዲተር በተመረመረ ሂሣብ ብቻ ኪሣራ የተሸጋገረ ቢሆንም ባለሥልጣኑ በማናቸውም ጊዜ በሚያደርገው ምርመራ የተሸጋገረውን ኪሣራ ትክክለኛነት አረጋግጦ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ ይችላል፡፡"

፪. በደንቡ ከአንቀጽ ፳፫ (፪) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ ተጨምረዋል፡፡

"፫. የግብር አስገቢው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ሲፈቅድ ከአንድ በላይ የንግድ ሥራና ቅርንጫፎች ከተቀጠሩ ሠራተኞች የሚሰበሰበውን የሥራ ግብር፣ ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀናሽ የሚደረገውን የሠንጠረዥ ‹‹ሐ›› ግብር፣ የሠንጠረዥ ‹‹መ›› ገቢ ግብር፣ ክፍያዎችን በአቅራቢያው ለሚገኝ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በማሳወቅ በግንባር ወይም በሦስተኛ ወገን በኩል ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ ሊከፍል ይችላል፡፡

፬. ከዚህ በላይ ለተመለከተው ንዑስ አንቀጽ አፈፃፀም ከአንድ በላይ ቅርንጫፎች ያሉት ግብር ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሲሰጠው ቁጥሩ ተመሣሣይ ሆኖ ለቅርንጫፎቹ መለያ እንዲሆን የተሰጠውን ተጨማሪ ምልክት ወይም ፊደል በመጠቀም እያስታወቀ ይከፍላል ፡፡"

፫. የደንቡ አንቀፅ ፳፫ (፫) እና (፬) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀፅ (፭) እና (፮) ሆነዋል፡፡

፫. ልዩ ልዩ ድንጋጌ

በአዋጁ የተለያዩ ድንጋጌዎች የክልልና የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ባለሥልጣናትን ሳይጨምር ‹‹የግብር ባለሥልጣን›› ወይም ‹‹የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን›› የሚሉ ቃላትና ሐረጎች በሙሉ ‹‹መሥሪያ ቤት›› ወይም ‹‹የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን›› በሚሉ ቃላትና ሐረጎች ተተክተዋል፡፡

፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2. The Tax Authority must audit the books of account showing loss until the declaration period of the next tax year. The loss can be carried forward if the tax payer has submitted books of account showing loss audited by external auditors and the tax Authority fail to verify the same.

3. Notwithstanding the provision of sub- article 2 of this Article the Authority at any time can carry out an investigation and make an adjustment on the loss carried forward."

2. After sub-article 2 of Article 23 the following new sub articles (3) and (4) are added.

"3.) Tax payers having more than one business or branch offices, with the permission of the Tax Authority can make payments of tax deducted from income of employees, withhold tax on schedule "C" payments, schedule "D" income; by declaring directly to the branch office of the Authority or through third party delegated by the Authority or through electronically communication system (E-Filing).

4.) For the purpose of sub-Article 3 a tax payer who have more than one business or branch can declare and pay tax to the nearest branch offices of the tax Authority by using his Tax Identification Number (TIN) with a pre-fix to distinguish each branch."

3. Sub-Article (3) and (4) of Article 23 are renumbered as sub-Articles (5) and (6).

3. *Miscellaneous Provision*

The phrases "Tax Authority" or "The Federal Inland Revenue Authority" excluding the Tax Authorities of Regional States and City Administrations found in the different provisions of the Regulation are here by replaced by the following phrases "Institution" or "The Ethiopian Revenues and Customs Authority", respectively.

4. *Effective Date*

This Regulation shall come in to force upon the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of March 2009.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA